## የአንጃ ታሪኩ ቃልኪዳን ማፍረስ፣ ክህደት፣ ለስልጣን መስገብገብና በአገርና በሕዝብ ላይ ከፍተኛ ወንጀል መፈጸም ነው።

ከሳሙኤል ዳዊት
ወላይታ ሶዶ፤ ኢትዮጵያ

### <u>አንጃ ምንድነው? ተግባራቱስ ምን ምን ናቸው?</u>

ወጣቱ ትውልድ እንዲያውቀው አንጃ ምንድነው? በአጭሩ አንጃ ማለት በአንድ ድርጅት ወይም ፓርቲ መዋቅር ወስጥ የሃሳብ ልዩነቶችን በግልጽ አቅርቦና ተወያይቶ ከማሳመንና ከማመን ይልቅ ያንን ሃሳብ በሚያራምዱ ጥቂት ስዎች ብቻ ተደብቆ ድርጅቱን በመቦርቦርና በመከፋፈል ተገንጥሎ የመውጣትና የማፍረስ ተግባር የሚያራምድ ማለት ነው፡፡ የአንጃ ዋና ዋና ተግባራት ብዙ ናቸው፡፡ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ቀድሞ የነበረበትን ድርጅት ለማፍረስ ውስጥ ለውስጥ መስራት፣ የድርጅቱን ደንብና ሕግ መጣስ፣ ለውይይት በር መዝጋት፣ ከድርጅቱ ተነጥሎ በመውጣት የድርጅቱን ሚስጥሮች ለጠላት መስጠት፣ በድርጅቱ ውስጥ በነበሩበት ወቅት የሚያውቁትን አባላት በማጋለጥ ለጠላት መረጃ ማቀበልና አደጋ ማድረስ፣ ከጠላት ጋር በመሆን የድርጅቱን አባላት መግደልና ማስገደል፣ ስለላ ማካሄድ ፣ ሕዝብን ለማወናበድ ከጠላት በሚሰጣቸው ድጋፍ ቀደም ብለው በነበሩበት ድርጅት ስም እንቅስቃሴ ማድረግ ወይም ተለጣፊ መመስረት፣በድርጅት ውስጥ ሆነው የውሸት መረጃዎችን በማናፈስ አባላትን ለመከፋፈል በልዩልዩ ዘዴዎች ጥረት ማድረግ የሚጠቀሱ ናቸው። የዚህ ሁሉ ጥፋት የመጨራሻ ግቡ ከጠላት ወግኖና ከእግሩ ስር ወድቆ ህዝብን ክዶ ስልጣን ለማግኘትና ፍርፋሪ ለመልቀም ነው። ይህ ለመሆኑ በተለያዩ ድርጅቶች የተፈጠሩትን አንጃዎች ታሪክ ማጤኑ አስፈላጊ ነው። በዚህ ትንሽ ጽሁፍ በኢሕአፓ ውስጥ ተፈጥረው የነበሩት አንጃዎች በድርጅቱና በአባላቱ ላይ የፈጸሙትን ወንጀልና በመጨረሻም የወገኑት ጠላት በዋናዎቹ የአንጃ መሪዎች ላይ የወሰደውን እርምጃ ባጭሩ አቀርባለሁ።

ይህን ጽሑፍ ለመከተብ ምክንያት የሆነኝ የወያኔ/ኢህአዴግ ሹም ወደ ሰሜን አሜሪካ በሄደበት ወቅት 'ለመጀመሪያ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሬ የምለው ሰው አገኘሁ' ያለው በ2007 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር የዛሬ 12ዓመት ከድርጅቱ ልዩ ጉባኤ ሊገኝ ሄዶ ከሌሊቱ 9 ሰዓት (3:00am) የጠፋውና ጥቂት ተባባሪዎቹን ይዞ አንጃ ፈጥሮ የነበረው ግለሰብ(መርሻ ዮሴፍ) ሶስት ግለሰቦችን ይዞ በሹሙ እገዛ ሕገወጥ ተግባር በመፈጸም በኢሕአፓ ስም አዲስ አበባ የገቡትና(በድርጅቱ አባልነት የማይታወቅ የኪራይ ዶ/ር ጭምር) በተለያዩ ጊዜ ከድርጅቱ ላይ አንጃ ፈጥረው የወጡ፣ የደርግ መንግስትና የውጪ አገር መንግስታት ሰላይ ሆነው ኢሕአፓንሲያጠቁና ሲያስጠቁ የነበሩ፣ የተሰዉት ጓዶች የሰጡትን አደራ የረሱና ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለአገራቸውየገቡበትን ቃል ኪዳን ለግል ጥቅምና ለስልጣን ጥም የሸጡ አንጃዎችና በ1984ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ ሔደው ፎረም 84ን ፈጥረው ለወያኔ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ የስልጣን ጥመኞችና ከሃዲዎች የኢህአዴግ ሹም ካድሬዎች ባዳረጉት እገዛና አባሎቻቸው በሞሉበት አዲስ አበባ ላይ አደረግን ባሉበት ስብሰባ ላይ የፈጸሙት ክህደት ነው።

### <u>አንጃ ከኢሕአፓ ወጥቶ ከደርግ ጋር</u>

ኢሕአፓ በወቅቱ ያቀረባቸውን በህዝብ ዘንድ ብዙ ድጋፍ የነበራቸው መሰረታዊ ጥያቄዎችን መሬት ላራሹ፣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ከሁሉም የህብረተስብ ክፍል ይመስረት፣ ዲሞክራሲ ያለገደብ ይፈቀድ፣ የሃይማኖት እኩልነት ይከበር፣ የሴቶች የእኩልነት መብት ይከበር፣ ትምህርት ለሁሉም በእኩልነት ይሰጥ፣ ሴክተር ሪቪው ይነሳ፣ ፍትህ ለሁሉም በዕኩልነት ይሁን፣ የሕግ የበላይነት ይከበር፣ ደርግ ወደ ምሽጉ ይመለስ ወዘተ በማለት ትግል በሚያካሄድበት ወቅት ወታደራዊ መንግስት ስልጣን ላይ ይቆይ ያለው በ1969 ዓም የተፈጠረው የመጀመሪያአንጃ አለኝ ያለውን ጥያቄ ለአባላት ድርጅቱ ልኮ ባለበት ወቅት ከድርጅቱ እውቅና ውጪ የድርጅቱን ደንብ ጥሶ ለውይይይት በር በመዝጋት አንጃ ፈጥሮ ተገኘ። ከዚያም የአንጃው ተከታዮች የደርግ አገዛዝ መሳሪያና ካድሬ በመሆን የድርጅቱን መዋቅር አጋለጡ፣ በድርጅቱ ውስጥ በነበሩበት ወቅት የሚያውቁትን አባላት ስም ዝርዝር፣ የድርጅቱን ንብረትና ገንዘብ ለአገዛዙ በመስጠትና በማጋለጥ፣ በግድያ ላይም በመሳተፍ በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ አደጋ አደረሱ። አባላት እንዲታሰሩ፣ የተለያዩ ሰቆቃዎች እንዲደርስባቸው፣ አገር ጥለው እንዲሰደዱ አደረጉ፤አስደረጉ።የደርግ ስርዓት ስልጣን ላይ እንዲቆይ ትልቅ ሚና ተጫውተው ኢሕአፓና ሕዝብ በተፈጸመው እመቃእንዲደካሙበማድረግ በአገር ውስጥሲንቀሳቀሱ የነበሩት ገንጣይ፣ አስገንጣይ፣ ሌሎች ጠባብና ዘረኛ ኃይሎች እንዲሁም የቅርብና የሩቅ የውጭ የኢትዮጵያ

ጠላቶች እንዲጠናከሩ አስተዋጽኦ አደረጉ።እንደ አጼ ቴዎድሮስ አንድ ጥይት እስከሚቀር ድረስ ኢትዮጵያን እከለከላለሁ ሲል የነበረው፣ የአገራቱን ምርጥ የጦር መሪዎች ገድሎ፤ ጦሩን ያለመሪ በማስቀረት፣ ከኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች በማበር አገር ጥሎ ወደ ዚምባቡዌ የሸሸው ኮሎኔል ያንን ጀግና ኢትዮጵያዊ ትውልድ ገድሎ ስልጣን ላይ እንዲቆይ አደረጉ፤ አገራችን አሁን ላላችበትምሁኔታ መድረስ የራሳቸውአስተዋጽኦ አለ።የመጀመሪያው አንጃ መሪብርሃነ መስቀል ረዳ ከድርጅቱ ተለይቶ በሰሜን ሸዋ የመሬትን አዋጅ ተቃውሞ ከነበረው ፊውዳል ጋር አብሮ ከመስራቱም ሌላ ለአገዛዙ እጅ ሰጥቶ በ120 ገጾች ድርጅቱን የሚያወግዝ ጽሁፍ አቅርቦ ነበር በወቅቱ የቴሌቪዝን መምሪያ ኃላፊ በነበረው ግለሰብ አማካይነት በሶስት ገጽ አጥሮ ለፋሽስቱ መንግስቱ ኃይለማርያም እንዲቀርብ ተደርጎ ነበር። ፋሽስቱ ግን ገደለው። የነበሩበትን ድርጅት ክዶ፣ለስልጣን መስገብገብና ከጠላት ጋር ማበር ውጤቱ ይህ ነበር።

## <u>አንጃ በኢሕአሠ ውስጥ</u>

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (በኢሕአሠ) ውስጥ አንጃ የተፈጠረው በአሲምባ ውስጥ ነበር። ይህ አንጃ በእነ ተስፋዬ መኮንን የተመራ የጥቂት ግለሰቦች ቡድን ድርጅቱን ክዶ ከደርግ በተደረገለት እርዳታ ማሊሪድ (ማርክስስት ሊኒኒስት ሪቮሉሽነሪ ድርጅት) የሚል ድርጅት መስርቶ ከደርግና በወቅቱ ከደርግ ጋር ከወገኑት ከመኢሶን፣ ከወዝሊግ፣ ከሰደድና ከኢጭአት ጋር በመሆን በኢሕአፓና ለውጥ ፈላጊው የሕዝብ ክፍሎች ላይ የዘመተ ነበር። ሁለተኛው በ1979 (1971ዓም) የተፈጠረው የተሰጠውን የሰራዊት ግዳጅ ወደ ጎን በመተው መደረግ የማይገባቸውን ስብሰባዎች በማካሔድ በድርጅቱ አመራር አባላት ላይ እርምጃ ለመውሰድ ሲያሴር የተገኘ ከመሆኑም በላይ፣ ሰራዊቱ እንዲበታተን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። በሰራዊቱ ውስጥ አንጃ እንዲፈጠር ዋናውን ሚና ሲጫወቱ የነበሩት የደርግና የወያኔ ሰላዮች መሆናቸው መጨራሻ ላይ በወሰዱት ስምሪታቸው ታውቋል። የደርግ ሰላዮች የነበሩት ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ስልጣን ላይ ተቀምጠው አገዛዙን አገልግለዋል። በመጨረሻም የወያኔ ሰላዮች የነበሩት ኢህዲን (የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ) የሚባል ድርጅት በማቋቋም የኢትዮጵያን ሕዝብ ልብ ለማግኘት ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ያለው ድርጅት መስሎ በመቅረብ ሙሉ በሙሉ በወያኔ ትእዛዝ እየተመራኢትዮጵያን በአደጋ ላይ ጣለ። ሲመራ የነበረውም በእነ በረከት ስምኦን በታምራት ላይኔና በመሳሰሉት ነበር። ዋና ዓላማም የኢሕአፓ ወኪሎች እኛ ነን በማለት ሕዝብን ማወናበድ ነበር ።የሰሩት ጥፋቶችም ብዙ ናቸው። ከወያኔ ጋር በማበር አገር ከፋፋይ የሆነውን የወያኔ ህግ መንግሥት ተግባራዊ እንዲሆን፣ የዘርና የቋንቋ ፌዴራሊዝም ን በአገሪቱ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን በማድረግ፣ በመለስ ዜናዊ ትእዛዝ ወደ ብአዴን(ብሔረ አማረ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) በመለወጥ በአማራ ወገኖቻችን ላይ ግድያ፣ እስረት፣ ማፈናቀል፣ የኢኮኖሚ ዝርፊያ፣ባጠቃላይም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፎች በኩል ከፍተኛ በደል ፈጽመዋል።

## <u>አንጃ ከወያኔ ጋር ለመሥራት ያደረገው ያላሰለሰ ጥረት</u>

በረከት ስምኦን የተባለው የዚህ ቡድን አባል በአማራ ሕዝብ ላይ ሲፈጽም ከነበረው ግፍ ሌላ በደቡቡ የአገራችን ልዩልዩ ክፍሎች ለመብታቸው የሚታገሉ ህዝቦችን ድምጽ ለማስገዛት ጦር አስዘምቷል።ለምሳሌ በ1992 ዓም (2000በፈረንጆች አቆጣጠር)በሀዲያ ዞን በተደረገው የተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ወቅት ሕዝቡ የተቃዋሚ ድርጅት አባላትን በመምረጡ በ1993ዓም(2001 በፈረንጆች አቆጣጠር) የዞንና የወረዳ ምክር ቤት አባላት ምርጫ ከመካሄዱ በፊት በዞኑ ውስጥ ባሉ ቀበሌዎችና ወረዳዎች ብዛት የጦር ሰራዊት በመመደብ የተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ በተካሄደበት ወቅት ትግል ያካሄዱ በነበሩ ታጋዮችና ተከታዮቻቸው ላይ እስር፣ ማፋናቀል፣ በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ ወሲባዊ ጥቃት በማድረስ፣ እንዲሁም ህዝቡን በማስፈራረት የሰነልቦና ሽብር በመፈጸም እስከ 1997ዓም ምርጫ ለማካሄድ ጥቂት ወራት እስከሚቀር ድረስ ለአራት ዓመታት ቆይቶ ከላይ በተጠቀሰው ግለሰብ በጎ ፈቃድ ከዞኑ እንዲነሳ ተደርጓል።

ይህ ቡድን በህዝብና በአገር ከፈጸመው ወንጀል ሌላ ኢሕአፓንለማጥቃት በከፍተኛ ደረጃ ተንቀሳቅሷል።የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ጽ/ቤት ባቋቋመው የኢሕአፓን እንቅስቃሴ በሚከታተለው ኮሚቴ ውስጥ አባል በመሆን፣ ከሰሜን አሜሪካ ከበደ ደስታና ብስራት መኩሪያ የተባሉ የኢሕአፓ አባላትን በገንዘብ በመግዛት ፎረም 84 የተባለውን ቡድን በመቋቋም በኢሕአፓ ላይ ጥቃት ለመፈጸም ቢሞክርም ኢሕአፓና አባላቱ ባደረጉት ጥንቃቄ በነበረበት ትግል ይህን የስልጣን ፈላጊ፣ አጫብጨብና ቅጥረኛ ቡድን ከጥቅም ውጪ እንዲሆን አድርገዋል። ጥቂቶች ግን ለወያኔ ታማኝ ሆነው በመገኘታቸው ለስልጣን በቅተው በአገራችንና በህዝባችን ላይ ከወያኔ ጋር በመሸረክ ትልቅ ወንጀል ፈጽመዋል። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣኑ ባላቤት ሲሆን መጠየቃቸው አይቀርም።

ይህ በበረከትና በወያኔ የደህንነት ኃላፊ ከነበረው ጌታቸው አሰፋ ጋር በመሆን በኢሕአፓ ውስጥ ሶስተኛ አንጃ ለመፍጠር በድርጅቱ ውስጥ በነበሩ ቅጥረኞቻቸው በኩል ብዙ ጥረት አድርገዋል። ኢሕአፓ ወያኔን ይቅርታ ጠይቆና አሺዳቢት ፈርሞ አገር ቤት መግባት አለበት የሚለውን ሀሳብ የሚያነሱ ግለሰቦች በድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ደረጃ በመፈጠራቸው ይህ ጉዳይ ለአባላት ወርዶ ውይይት በአባላት ተደርጎ ያነሱት ሀሳብ ውድቅ ሆኗል። በአባላት ሀሳባቸው ውድቅ የሆነበት ምክንያት የኢትዮጵያና የሕዝቧ ቁርጠኛ ጠላት የሆነውን ወንጀለኛውንና ከሃዲውንወያኔ፤ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ለኢትዮጵያና ለህዝቧ ጥቅም የቆመው ኢሕአፓ ይቅርታ መጠየቅ የለበትም። ይህ የሽንፈትና የተንበረካኪነት ሀሳብ ነው በማለት ነው። ግለሰቦቹ የአመራር ኮሚቴ ውስጥ ከሚያነሱት ጥያቄ ሊቆጠቡ ባለመቻላቸው ጉዳዩ ለአባላት እንደገና ቀርቦ አባላት አስቸኳይ የድርጅቱ ልዩ ጠቅላላ ጉባኤ ተካሄዶ ለጉዳዩ እልባት እንዲሰጥ በወሰኑት መሰረት በጥቅምት ወር

1998ዓ/ም (2007 በፈረንጆች አቆጣጠር) የድርጅቱ ጉባኤ በሚካሄድበት ወቅት መፍትሔ እንዲገኝ ያቀረቡትን ጥያቄዎች ሳያቀርቡ የሶስተኛው አንጃ መሪ አቶ መርሻ ዮሴፍ በውድቅት ሌሊት ከነበረበት ሆቴል ሲጠፉ፤ የቀሩት ጥቂቶችም በጉባኤ ላይ ቀርበው ሀሳባቸውን ሳያቀርቡ የድርጅቱን ደንብ ጥሰው ስብሰባውን እረግጠው ወጥተዋል። ከዚያም ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በማለት በድርጅቱ ላይ ተላጣፊ አቋቁመው ኢሕአፓንና ኢትዮጵያን ለመጉዳት ከሚሰሩ ሬዲዮ ጣቢያዎች ጋር በመቅረብ በድርጅቱ ላይ ዘምተዋል። ብዙ ሳይቆዩም ተከፋፈሉ። አንዴ ኢሕአፓ ትንሳኤሌላ ጊዜ ኢሕአፓ አንድነት በማለት ሕዝብን ለማወናበድ ሞከሩ። የትም መድረስ አልቻሉም። ከበረከት ስምኦንና ከወያኔ ደህንነት ኃላፊ ጌታቸው አሰፋ ጋር ግንኙነት ፈጥረው ከወያኔ ጋር ለመስራት ጥያቄ ቢያቀርቡም መለስ ዜናዊ አይረቡም በማለት ሊቀበላቸው ፈቃደኛ ባለመሆኑ በአየር ላይ ቀሩ። ከዚያም ከድርጅት ወደ ድርጅት በመዝለል ሸንጎ የሚባለውን ድርጅት መስርተው ከወያኔ ጋር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለመስራት የጣሩ ጉዶች ነበሩ።ይህን ኢሕአፓ( ዲ= ዲሞክራሲያዊ)በሚል ስም ህዝብን ሲያወናብድ የነበረውን አንጃ ሎጎ፣ አርማ፣ ሕጋዊ ሰውነትና በዋሸንግተን ጽ/ቤት ያለው እውነተኛው ኢሕአፓ በፍርድ ቤት ከሶ ከሕገወጥ ድርጊታቸው አስቁሟል።ይህ ከሃድ፣ የስልጣን ፈላጊና ሴራኛ የጥቂቶች ጥርቅምሸንጎ በሚባል ድርጅት ዙሪያ በሚሽከረከሩበት ወቅት ነው የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስቴር ነኝ ባይ የወያኔ ሹም ዲሲ በመጠበት ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስቴሬን አገኘሁ ያለውን ከ12ዓምት በፊት ከድርጅቱ ከወጣሁ አንጃ መሪ ከመርሻ ዮሴፍ ጋር በመመሳጠር በኢሕአፓ ስም አገር ቤት እንዲገባ ሁኔታዎችን አመቻችቶ የጋበዘው።

## <u>የአንጃ የሥልጣን ስግብግብነት ከገዳይና አገር አጥፊ ጋር አብሮ ለመሰለፍ የሚያደርገው ሩጫ</u>

ለ28ዓመታት የወያኔ/ኢህአዴግ አገልጋይ በመሆን፣ የስለላ ተቋሙ (ኢንሳ = የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ) ከፍተኛ ባለስልጣን ሆኖ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ስልክና ኢሜል በመጥላፍ ከፍተኛ ሰቆቃ እንዲፈጸም ባደረገው፣280 የሬዲዮ ጣቢያዎች፣ ቴሌቪዥን ጣቢያዎች፣ ድረገጾች፣ ሌሎች ብዙሃን መገናኛዎችን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይጠቀም በመጥለፍና በመዝጋት ትልቅ ሚና በነበረው፣ ባሁኑ ወቅት የአሜሪካና የምዕራባውን፣ የሳውዲ አረቢያ፣ የኳታርና የአረብ ኤሜሬትስ ጥቅም ለማስጠበቅ በቆመው በአቢይ አገዛዝ ስር አገሪቱና ህዝቧ ለአገርና ለውጭ ጠላቶች ተጋልጠው በሚገኙበት ፣በጽንፈኞችና በአገዛዙ የጸጥታ ኃይሎች ድጋፍ በወገኖቻችን ላይ ግድያና ጭፍጨፋ በግፍ በሚፈጸምበት፣ በአገራችን ታሪክ ታይቶና ተፈጽሞ የማይታወቅ ወገን በወገን የማያደርገው ሰው ገድሎ አስካሬን መንገድ ለመንገድ በሞተር ብስክሌት በሚጎተትበት፣ በግፍ የተገደሉ ዜጎቻችን አስካሬን በተወለዱበት አካባቢ አይቀበርም፤ ሌላ ቦታም መወሰድ አይቻልም፤ ለጅብ ነው መስጠት ያለበት በሚባልበት፣ ሰው እግር ወደላይ አንገት ወደታች ተደርጎ ተሰቅሎ በሚገደልበት፣ ለዘመናት ያፈሩት ሀብትና ንብረት በሚወድምበት፣ በእምነት ተቋማት ላይ ቃጠሎ በሚፈጸምበት፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ብዙ ዘመን ከኖሩበት ቀዬ በሚፈናቀሉበት፣በዜጎቻችን ግድያ፣ ጭፍጨፋና ሌሎች ወንጀል በፈጸሙ ግለሰቦች ላይ እርምጃ በማይወስድበት፣ ፍትህ፣ ሕግና የሕግ የበላይነት በሌለበት፣ የስርዓቱ አፈኝና ሌሎች የሽብር ህጎች ባልተነሱበት፣ የሰውን የመነገር መብትየሚከለክል ረቂቅ አዋጅ እየተዘጋጀ በሚገኝበት፣ ኢህአዴግ የተባለው የግፈኞች ስብስብ ድርጅቱ አመራር ላይ ያሉ ግለሰቦች ላይ ለውጥ ሳያደርግ ግፉን ለመቀጠልና የለመዱበትን ውንብድናና ወንጀል በህዝብና በሀገር ላይ ለማካሄድ የብልጽግና ፓርቲ መሰረትን ብለው የስም ለውጥ ብቻ በማድረግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለስልጣን የሚያበቃውን የሽግግር መንግስት ጥያቄ እምቢ ተብሎ ባለበት፣ ለ28ዓመታት ሙሉ በውሸት ስልጣን ላይ ለመቆየት የተጠቀሙበትን የቧልት ምርጫ ለማካሄድ ዝግጀት በሚካሔድበት፣ ኢኮኖሚው ወድቆ የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ እጅግ አስቸጋሪ በሆነበት፣ ለአገር ዕድገትና ስልጣኔ በሁሉም መልኩ ወሳኝ ሚና የሚጫወተው ትምህርት ክህሎትና እውቀት ያላቸው ዜጎች እንዳይመረቱ የትምህርት ሁኔታ ከድጡ ወደ መጡ እንዲሆን የትምህርት ፖሊሲ ቀረጻ ባለሙያዎችን አግልሎ በወያኔ/ኢህአዴግ ካድሬዎችና ኢትዮጵያን ጥገኛቸው ለማድረግ በሚፈልጉ የውጭ ኃይሎች ሆን ተብሎ አገርን ለመጉዳት በእቅድ በሚሰራበት፣ ዜጎች በአገራቸው የጤና አገልግሎትና መድኃኒት ሊያገኙ በማይችሉበት፣ ከቦታ ቦታ ዝውውርና እንቅስቃሴ በተገደበበት፣ የሲቪክና የሙያ ማሕበራት በነጻነት የመደራጃት መብታቸው በተነፈገበት፣ የመምህራንና የተማሪዎች የአካዳሚክ ነጻነት በተከለከለበት፣ በተለያዩ በእገሪቱ ባሉ ዩኒቨርስቲዎች ዘርን መሰረት ያደረገ ግድያ በሚካሄድበት፣ በየዩኒቨርስቲዎቹ የትምህርትና ሌሎች አገልግሎቶች በማይሰጥበት፣ ኢትዮጵያን ታሪክ አልባ ለማድረግ ወጣቱ የእገሪቱን ታሪክ እንዳያወቅ በተረኞች የአገሪቱ ታሪክ ሆን ተብሎ በሚደልዝበትና የውሸት ታሪክ በሚዘጋጅበት ባሁኑ ወቅት ይህ በአገርና በሕዝቡ ላይ የሚፈጸመው ግፍና ወንጀል ከቁም ነገር ውስጥ ያላስገባው የኢሕአፓን ስም ሰርቆ ወደ አዲስ አበባ የገባው የአንጃ ቡድን በቮልት ምርጫእሳተፋለሁ በማለት ተረኞች የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲያጠቁ የበኩላቸውንየተላላኪነት ሚና ለመወጣት በመቅበዝበዝ ላይ ናቸው። ይህ አንጃ በኢሕአፓ ታሪክ የማይታወቀውን የድርጅቱ የበላይ ጠባቂ(መሪ)፣ ሊቀመንበር የሚሉ ርዕሶችንለማያዝ ያላቸውን ፍላጎትና የስልጣን ስግብግብነት አሳይተዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ ያለበት በኢሕአፓ ውስጥ ዋና ጸሓፊ ሆኖ ለተወሰኑ ዓመታት ሲያገለግል የነበረው ግለሰብ(ብርሃነ መሰቀል ረዳ) ከድርጅቱ የጋራ ውሳኔ ውጭ በግሉ ኃላፊነት ሳይሰጠውየተለያዩ ጉዳዮችን ሲፈጽም ከተገኘበት ወቅት ጀምሮኢሕአፓ ቢያንስ ለ43 ዓመታት የሚመራው በከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ነው። ድርጅቱ ሊቀመንበር የለውም።ይህ አሰራር በድርጅቱ ውስጥ አምባገነኖችና ተክለ ሰውነት ፈላጊዎች እንዳይፈጠሩ ጠቅሞታል።

በድርጅቱ ውስጥ በየጊዜው የተፈጠሩ አንጃዎች በሙሉ ሊቀመንበር፣ሊቀመንበር ሲሉ ነበር፤ ድርጅቱ ሊቀመንበር ይኑረው ይሉ ነበር። ዓላማቸው ተክለሰውነት ለማገንባትና የድርጅቱ ሊቀመንበር ነኝ በሚል ጉራ ለጠላት ራሳቸውን ለመሸጥና ያን ስም በመያዛቸው ከጥፋታቸው የሚያመልጡ መስሏቸው ነው ። ያ ደግሞ በመርሻ ዮሴፍ በኩል በተግባር ታይቷል። በቅርቡ የአንጃውኢሕአፓ ሊቀመንበር የተባለው አጭበርባሪ ጳውሎስ ሶርሳ በኢሕአፓ ውስጥ ሰርጎ የገባ የደርግ ሰላይ ነበር። በስምሪቱም ብዙ የድርጅቱን አባላት በሸሸመኔ፣ በወላይታና በሌሎች ቦታዎች ያስፈጃ አረመኔ ነው። በደቡቡ የአገራችን ክፍል ድርጅቱ ወታደራዊ ቤዝ ለመመስረት እንቅስቃሴ በሚያካሄድበት ወቅት የአካባቢው ሰው በመሆኑ ለድርጅት ስራ በተንቀሳቀሰበት ቦታዎች ሁሉ ድርጅቱን ለአደጋ የጣለ ነው። በ1984 ዓም በተመሰረተው ፎረም 84 ቡድን ውስጥ አባል በመሆን ጸረ- ህዝቡን ወያኔ አገልግሏል። ይህን የሕዝብና የአገር ጠላት የሆነውን ግለሰብ ኢትዮጵያውያን ማወቅ ይኖርባቸዋል።ከማህበራዊ ግንኙነቶችማራቅ፣ ማጋለጥናበሕዝብ ልጆች ላይ ላደረሰው የግድያ ወንጀል ተባባሪነት የእጁን እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል። በእሱ ቤት የፈጸመው ወንጀል የሚደበቅና የማይታወቅ መስሎታል። ከህዝብና ከኢሕአፓ አይታ የሚሳወር ምንም የለም።

***<u>ሀሰት ወይም ውሸት ማስራጨት የአንጃ አንዱ ባህሪ መሆኑ</u>***

የአንጃው የበላይ ጠባቂ የተባለችው ቆንጅት ብርሃኔም የኢሕአፓ አባላትንና ከጎኑ የነበረውን ሕዝብ የገደሉትን ሁሉ (ደርግን፣ ወያኔን፣ መኢሶንን፣ ገዳይ ከዲሬዎችንና ሌሎችንም) ይቅርታ በመጠየቅ ኢሕአፓን ተጠያቂ አድርጋለች፣ኢህአፓ አባል ባልነበረበት ሸንጎ የተባለው ድርጅት ውስጥም አባል ሆኖ ሰርቷል በማለት ዋሽታለች፣አባል ሆኖ የሰራው ኢህአፓ(ዲ) የተባለው ተላጣፊ አንጃ የፈጠረው ድርጅት ነው።ሸንጎ ለወያኔ አገልግሎት ለመስጠት ያለቅድመ ሁኔታ አገር ቤት ለመግባት ይፈልግ የነበረ የአስመሳዮችና የስልጣን ጥመኞች ጥርቅም እንጂ የትግል ድርጅት አልነበረም።ታጋይ ያልነበረ ድርጅትን ታጋይነበር በማለት ህዝብን አታልላች፣ ባልነበረችበት ጉዳይ ለስልጣን ብላ የአንጃን የውሸት ተልዕኮ ፈጻሚና ተባባሪ ሆና ታገኝታለች።አንጃም ሆናለች። በህዝብ ልትርቅና ልትጋለጥ የሚገባት ናት። በቁሮ መንጋና በአገዛዙ ባለስልጣናትትብብር በቤታቸው፣ በመንገድና በዕምነት ተቋማት ተጠልለው ይኖሩ በነበሩ ሰላማዊ ዜጎቻችን ላይ የግድያና የጭፍጨፋ እርምጃ በወሰዱ ጽንፈኞች ላይ አቢይ ተመጣጠኝ እርምጃ ሳይወስድ በሁለት ተፈላሚ ወገኖች የተደረገ ይመስል“በግጭቱ” ሰዎች ሞተዋል በማለት የተጠቀመበትን ቃል በመጠቀም “በግጭቱ የተሳተፉ ለፍርድ ይቅረቡ” የሚል ርዕስ መግለጫ በመስጠት በቆንጅት የሚመራው አንጃ በወገኖቻችን ስቃይ ተሳልቆ የሹሙ ደጋፊ ሆኖ ተገኝቷል።የአገዛዙ ተላላኪነት ከዚህ የበለጠ ምን መለያ ይገኛል።ብዙዎቹ ለእውነተኛ ጋዜጠኝነት ሙያ ክብር ያላቸው ጋዜጣኞች እሳትን ለቀው እውነተኛ መረጃ ለኢትዮጵያ ህዝብ በሚያደርሱበት ባሁኑ ወቅት፤ ብርሃኑ ነጋ የአፈ ቅቤውና የልበ ጩቤው የወያኔ ጠ/ሚኒስቴር የአቢይ ደጋፊ በመሆን በኢሕአፓ ላይና በሌሎች ለህዝብ በቆሙ ክፍሎች ለምሳሌ በባልደረስ ም/ቤትና በመሪው እንዲሁም በቁሮ መንጋ በአገዛዙ የጸጥታ ኃይሎች ትብብር በወገኖቻችን ላይ የደረሰውን ግድያና ጭፍጨፋ ላይ የውሸት መግለጫና አስተያየት በመስጠት አርአያቸው ሆኖ ከመገኘቱም ሌላ የሚያዛቸው በአዲስ አበባና በዋሽንግተን ዲሲ ራሱን “የኢትዮጵያ ህዝብ ዓይንና ጆሮ” ብሎ የሚጠረው የእሳት ጋዜጣኞች ለተረኛ አገዛዝ መሳሪያ በመሆን ህዝብ እውነቱን እንዳያውቅ የውሸት ዜና በማቅረብ የአጭበርባሪነት ሚናቸውን እየተወጡ ነው። አይ እሳት ድንቄም የኢትዮጵያ ህዝብ ዓይንና ጆሮ። ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ብትቆሙ ይሻላል።ከስህታተችሁ አንማርም ብላችሁ ነው እንጂ የውሸት መጨረሻው ከሕዝብ መነጠልና ውርደት መሆኑን ለማወቅ ብዙ ጊዜ ነበራችሁ። በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘው የእሳት ክፍል የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባላት ከብዙ ዓመታት በፊት በጣቢያው የሰጡትን ቃለመጠይቅ መለልሶ በሚያቀርብበት በአዲስ አበባ የሚገኘው የእሳት የመከሊት ፕሮግራም አዘጋጅ ጋዜጠኛ የኢሕአፓ መሪ ብሎ ለጋበዛት የአንጃ መሪ ለቆንጅት ብርሃኔ “ ኢሕአፓ አሲምባ ሲገባ የመከረው የት ነበር?” የሚል ጥያቄ አቅርቦ ነበር። የቆንጅት መልስ ግን ኢሕአፓ አሲምባ ሲገባ ውጭ አገር ነበረ የሚል ነው። በፍጹም ስህተት ነው። አሲምባ የገባው ኢሕአሠ (የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት) ነው። የተመሰረተውም በ1964ዓም በሚያዝያ ወር በጀርመን በርሊን ከተማ ለአገራቸው ኢትዮጵያና ለሕዝቧ ቀናኢ የሆኑ ለውጥ ፈላጊ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያ፣ ከአውሮፓ፣ ከሰሜን አሜሪካ፣ ከአፍሪካና ከሌሎች የዓለም ክፍሎች ተሰብስበው በመሰረቱትኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ድርጅት (ኢሕአድ) ስር ነው። ኢሕአፓ አሲምባ አልገባም፤ ውጭም አልነበረም። አብዮትና ቀይባንዲራ በመባል ከሚታወቁ አብዮታዊ ክፍሎች ከኢሕአድ ጋር ብዙ ውይይት ከተደረገና ስምምነት ከተደረሰበት በኋላ ውህደት አድርገው ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ(ኢሕአፓ)ን መሰረቱ። የፓርቲው ምስረታና ፕሮግራሙ በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ እንዲሁም በእንግሊዝኛ ለህዝብ ይፋ ተደርጓል። ሰራዊቱ ግን ኢሕአሠ የሚለውን ምዕጻረ ቃል ይዞ ኢሕአፓ ከተመሰረተ በኋላ ከድርጅቱ ስር ቆይቷል። ጠያቂውም ሆነ “የኢሕአፓ መሪ” ተብዬ አንጃ ቆንጅት ኢሕአፓን አታውቁም። በመሆኑም ስህተት መረጃ በመስጠት አሳስታችኋል። ኢሕአፓ አእላፍ አባላት የነበሩበት ዛሬም ያሉበት ድርጅት ነውና ማንም አንጃና ውሸት አሰራጭ ጋዜጣኛ ነኝ ባይ ግለሰብ ታሪኩ የሚደልዝበት አይደለም። ኢሕአፓን ለቀቅ አድርጉና ለቋመጣችሁበት ስልጣን ከተረኞቹ የሕዝብ ጠላቶች ጋር ተሞደሙዱ።

***<u>ማጠቃለያ</u>***

ባጠቃላይ የሹሙን እግር ልሶ አገር ቤት ገብቶ በኢሕአፓ ስም የሚነግደው አንጃ ከዚህ በፊት ወያኔን ይቅርታ በመጠየቅና ደብዳቤ በመጻፍ አገር ቤት ለመግባት ሲለምን የነበረ በመሆኑ፣ ለአገርና ለህዝብ የሚፈይደው ስለሌላ በጠላትነት ፈርጆ ጥቃት ማድረስ ከህብረተሰቡ ይጠበቃል።በየጊዜው የተፈጠሩት አንጃዎች የነበሩበትን ድርጅት፣ አባላት፣ አገርና ህዝብ ሲክዱ፣ ቃል ኪዳን ሲያፈርሱ፣ ለስልጣን ሲስገበገቡና

በአገርና በሕዝብ ላይ ወንጀል ሲፈጽሙ እንደነበር በሰነድ የተረጋገጠ ስለሆነ፤ምንም እንኳን ህዝብን ለማጭበርበር የአሁኖቹ አንጃ ከአገዛዙ ጋር በማበር የኢሕአፓን ስም ሰርቆ ቢጠቀምም ከዚህ በፊት ላደረጉትም ሆነ አሁን በማድረግ ላይ ለሚገኙት ወንጀል ከተጠያቂነት ሊድኑ አይችሉም። 'አይነጋ መስሏት ....... ' እንደተባለው ተደብቆና ተረስቶ ተሸፋፍኖ የሚቀር ነገር የለም፡፡ ሕዝብም የጠላት መሳሪያና ተባባሪ በመሆናቸው ማነነታቸውን አውቆና ተረድቶ ተገቢውን ቅጣትና ፍርድ እንደሚሰጣቸው ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

**አንጃ ግራንጃ ከወያኔ ጋር አብሮ ይወድማል!!**

**የኢትዮጵያሕዝብ ሁሉንም ጠላቶቹን አሸንፎ የድሉ ባላቤት ይሆናል!!**

**ለሽግግር መንግስት ምስረታ ትግሉ ይቀጥላል!!**